# ብቸኛው እስረኛ

ቀደም ሲል፣ በደርግ ዘመነ መንግሥት የሠረዊቱ ስንቅ ማደራጃ ሆኖ ያገለግል ነበር። ኢህአደግ ሥልጣን እንደያዘ ቂም የያዘባቸውንና ጠላቶቼ ብሎ የፈረጃቸውን ሰብስቦ አጎረበት። ቃሊቲ እስር ቤት ወይም በዘመናዊ ቋንቋ ማረሚያ ቤት ይባላል። አብዛኛው እስረኛ በደርግ ዘመነ መንግስት ሥልጣን ላይ የነበረ ወይም የመከላከያ ሠራዊት አባል ነው። ወያኔ ሥልጣን በያዘ በሁለተኛው ዓመት መልሶ በተቋቋመው አየር ኃይል ሥራ ላይ የነበሩ፤ ለኢትዮጵያ አየር መንገድ ይበሩ ከነበሩት ውስጥ እንዲሁም በሌላ ሥራ መተዳደር ከጀመሩት የቀድሞ አየር ኃይል አባላትን ጨምሮ በጦር ሜዳ ወንጀል ክስ ተጠያቂ ናችሁ በሚል ሰበብ ዘብጥያ አወረዳቸው።

የቃሊቲ እስር ቤት በመጀመሪያ ከታሰሩት ውስጥ ዛሬ አብዛኛው እስረኛ ነፃ ወጥቷል። ቢያንስ በትንሹ ሰባት አመት እስር ሳይቀምስ የተለቀቀ ትንሽ ነው። ሌላው ግዜውን ይጠብቃል፣ አዲስ እስረኛም በየግዜው ይቀላቀላል። የቆየው አዲሱን ያለምዳል፣ ያጽናናል። ለአዲሶቹ እስረኞች ግን ለየት የሚሉ ሁኔታዎች እንደሚገጥሟቸው የታወቀ ቢሆንም እንደ አንድ አዛውንት ሁኔታ ግን ቀልባቸውን የሚስብ የለም። ቁመታቸው መካከለኛ ሆኖ የዳበረ ሰውነት ያላቸው፤ እድሜያቸው ወደ ሰባዎቹ የተጠጋ፤ የፊታቸው ፂም አድጎ ደረታቸው የደረሰ ከመሆኑ በላይ እንደወተት የነጣ ነው። ለመጀመሪያ ግዜ አይኑን የጣለባቸው እስረኛ የእስር ቤቱ ንስሃ አባት ይሆኑ? ብሎ እራሱን መጠየቁ የማይቀር ነው፣ ቄስ ብቻ ሳይሆን እንደውም ጳጳስ ናቸው ቢባል፤ እዚህ ምን ያደርጋሉ ይባላል እንጂ ምንም አያጠራጥሩም። ውሎ አድሮ ግን ስለኚህ አዛውንት ማንነት ሲታወቅ አዲሱ እስረኛ ላይ የሚደርስበት እግርሞት በቃላት ለመግለፅ ያስቸግራል።

ብርሃነ መስቀል ኃይሌ ይባላሉ። የቀድሞ አየር ኃይል ባልደረባ፤ ኮሎኔል፤ ፓይለት! ዛሬ ላያቸው ከእስር በፊት የነበራቸውን ህይወት ከአሁኑ ጋር ለማቀራረብ በጣም ይቸግራል። በልጅናታቸው የዘመናዊ ት/ቤት የጀመሩት እድሜያቸው ለትምህርት ካለፈ በኋላ ነው። ግና ከ1 እስከ 8ኛ ክፍል የሚሰጠውን ትምህርት የጨረሱት፣ እያጠፉ በማለፍ በ4አመት ውስጥ ብቻ ነበር። የቀረውን የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቻውን በተፈሪ መኮንን ት/ቤት በጥሩ ውጤት ካጠናቀቁ በኋላ እ.ኤ.አ በ1960 ዓ.ም የኢትዩጵያ አየር ኃይል ለበረራ መልምሎ ከሚያሰለጥናቸው የ11ኛ ግዜ ተወዳዳሪዎች(P-11) አንዱ ሆኑ። የበረራ ትምህርታቸውንም በጥሩ ሁኔታ ካጠናቀቁ በኋላ የበረራ ክንፋቸውን በ1961 ዓ.ም ከግርማዊ ቀ.ኃ.ሥላሴ እጅ ተቀብለዋል። ከዚያም በተለያዩ የአየር ኃይል ስኳድሮኖች ውስጥ በመመደብ የበረራ ግዳጆችን አከናውነዋል።

የምድር ጦር አየር ክፍል (አርሚ አቬሽን) በአዲስ ሲቋቋም ክፍሉን እንዲያቋቁሙ ከተላኩት የአየር ኃይል አባላት አንዱ ነበሩ። በዚህም ምድባቸው የተለያዩ አውሮፕላኖችን በመብረር ግዳጃቸውን የተወጡ ሲሆን የአየር ክፍሉ በሠራዊቱ ‘እናት’ እየተባለ እንዲጠራ አስተዋፅኦ ካደረጉት አባላት አንዱ ናቸው። ደርግ ለመጀመሪያ ግዜ ተዋጊ ሄሊኮፕተሮችን ወደ ሀገር ውስጥ ሲያስገባ፣ ሄሊኮፕተሮቹን ለማብረር ከተመረጡት አብራሪዎች አንዱ በመሆን እንደገና ወደ ቀድሞ ክፍላቸው ወደ አየር ኃይል ተመልሰው በተዋጊነትና በአስተማሪነት ይህ ቀረው የማይባል አኩሪ ሙያ ፈፅመዋል። የሀገራችንን የኢትዮጵያን ህልውና ከሚፈታተኑ የሀገር ጠላቶች ጋር ተናንቀው አኩሪ የጀግንነት ሙያ አስመዝግበዋል ስለዚህም የኢትዮጵያ ጀግና ሜዳልያ ተሸላሚ ለመሆን በቅተዋል።

ኰሌኔሉ ያላቸውን የሀገር ፍቅር በቃላት ለመግለፅ ያስቸግራል ቢባል ማጋነን አይሆንም። የኢትዮጵያን ታሪክ ጠንቅቀው ያውቃሉ። መተረክ ሲጀምሩ አድማጫቸው ብዙ ነው። ከሳቸው ጋር ቁንፅል ታሪክ አዋቂዎች መከራከርን አይደፍሩም። ታሪክ ብቻ ሳይሆን የሀገራችንን ወግና ባህል በሚገባ ያውቃሉ። የዚህ ሁሉ ባለውለታ የወንድ አያታቸው እንደሆኑ ይናገራሉ።

አያታቸው ሸንጐ ሲቀመጡ ወይም አመሻሽ ላይ ከመሰል ሽማግሌዎች ጋር ተቀምጠው ሲያወጉም ሆነ በአንዳንድ ቁም ነገር ላይ ሲከራከሩ፣ ትንሹ ብርሃነመስቀል ከአያታቸው እግር ስር አይጠፋም። አያታቸው ይህን የሚያደርጉት የልጅ ልጃቸው የሃገራቸውን ታሪክና ባህል ጠንቅቀው እንዲያውቁ ነበር። ይህ የልጅነት ተመክሮ በኰሌኔሉ ላይ ከፍታኛ የሀገር ፍቅር እንዲያድርባቸው አድርጓል። ጭፍን ፍቅር ብቻ ሳይሆን በታሪክና በማስረጃ የተደገፈ ስለሆነ በዚህ ጉዳይ ከሳቸው ጋር ለመወያየትም ሆነ ለመከራከር አባዛኛዎቹ የሥራ ጓደኞቻቸው አይደፍሯቸውም። የዚህ ፅሁፍ መግቢያ ላይ ቄስ ወይም ጳጳስ ናቸው ብለው የገመቱት አዲስ እስረኞች ብዙም አልተሳሳቱም። ኰሌኔሉ የቤተ ክህነት ትምህርት ጠንቅቀው ያውቃሉ። ይህ ጉዳይ ሲነሳ አንድ ገጠመኝን ማንሳት የግድ ይላል። እ.ኤ.አ በ1978 ዓ.ም ለሚ-8 ሄሊኮፕተር ትምህርት ከመሰል የሥራ ጓደኞቻቸው ጋር ወደ ቀደሞው ሶቭየት ህብረት ሲሄዱ ተሳፍረውበት የነበረው ኤሮፍሎት አየር መንገድ አውሮፕላን ውስጥ ጥቂት ሩሲያውያንና ሁለት ሌላ ኢትዮጵያውያን ነበሩ፣ ከሁለቱ ኢትዮጵያውያን አንዱ ቀሲስ ሦሎሞን ይባላሉ። በመንፈሳዊ ትምህርት የላቀ ደረጃ የደረሱ ሲሆኑ አብዛኛውን ትምህርታቸውን የተከታተሉት በቀድሞው ሶቭዬት ህብረት ውስጥ ነው። ለዚህ ጉዞአቸው ምክንያት ግን አብረዋቸው ይጓዙ የነበሩት ጳጳስ በሩስያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስትያን ለስራ ጉብኝት ተጋብዘው ለሳቸው አስተርጓሚ ሆነው ነበር የሚሄዱት። ታዲያ መሀል መንገድ ላይ ቀሲሱ መቀመጫቸውን ለቀው ወደ አርሚ አቪዬሽን መኮንኖች ቀረቡና ሰላምታ ከተለዋወጡ በኋላ ጨዋታ ይጀምራሉ። ቀሲስ ሰሎሞን ወቅቱ በሩስያ የብርድ ወር እንደሆነ እና ጥንቃቄ እንደሚያስፈልግ ፣ ሲቻል ቮድካ መጐንጨት ለብርዱ መፍትሄ እንደሆነ እንደቀልድ እየጠቆሙ ፣ ቀጥለውም ኢትዮጵያዊ ዘር ወዳለው እውቅ የሩስያ ገጣሚ የአሌክሳንደር ፑሽኪንን ታሪክ አንስተው ካወጉ በኋላ ከግጥሞቹ በቃላቸው እያነበነቡ ትርጉሙን በሚጥም አማርኛ አስከተሉ። ንግግራቸውን ጋብ አድርገው ለሌሎቹ እድል ሲሰጡ...... ኰሌኔል ብርሃነ መስቀል በረራን በተመለከተ ከመፅሃፍ ቅዱስ ንጉሥ ዳዊትን እየጠቃቀሱ በግእዝ አቸገጉደጎዱት። ጳጳሱም ሆኑ ቀሲስ ሰሎሞን ጆሮዋቸውን ማመን አቃታቸው። ከፓይለቶቹ ከናፍር ይህ ይወጣል ብለው ስላልጠበቁ እንደጉድ ተደነቁ። ኧረእስቲ አባታችን ጐን ይቀመጡና ያጫውቱን ሲሉ ቀሲስ ሰሎሞን ጋብዘው ወደነሱ ወደነበሩበት መቀመጫ ወሰዱዋቸው። አውሮፕላኑ ሞስኮ እሲኪያርፍ ኰሌኔሉ ወደ ጓደኞቻቸው አልተመለሱም።

እውነተኛ የሀገር ፍቅራቸው ከወያኔ ጋር ሊያስማማቸው አልቻለም። ሀገርን በተመለከተ ከመንግሥት ጋር ሆድና ጀርባ ሆኑ። የአቃቂ እስር ቤት ሀላፊውም አቋማቸውን ለማወቅ ግዜ አልፈጀበትም ምክንያቱም እርሳቸው ዘንድ ፍርሃት የለም። ፊትለፊት ነው የሚናገሩት ። ከሀገራቸው በላይ ምንም ነገር የለም። በፀባያቸው እልኸኛ ናቸው። የሀገራቸው ጉዳይ እንቅልፍ ነስቷቸው ካደረ በጠዋት ወደ ኃላፊው ቢሮ ሄደው ስለ ኢትዮጵያ አንድነት መፈክር ያሰማሉ፣ ወያኔን ያወግዛሉ። ለተወሰነ ቀን በእግረ-ሙቅ ታስረው ይቆያሉ። ይፈታሉ። ከጥቂት ቀናት በኃላ ያው ይደገማል የእስር ቤት ሀላፊው አልፎ አልፎ ጣል የሚያደርገው አባባል አለ። ‘ስማ ብርሃነ መስቀል! እዚህ እስር ቤት መጨረሻ የምንቀረው እኔና አንተ ነን ’ ይላቸዋል። ይህ አባባል ታዲያ ቀልድ መሆኑ ቀርቶ እውን እየሆነ ሄደ። አብረዋቸው ታስረው የነበሩ በርካታ የቀድሞው አየር ኃይል አባላት ዘሬ አንድም ከእርሳቸው ጋር የሉም። በሙሉ ከእስር ተለቀዋል። ብቸኛ የአየር ኃይል እስረኛ ናቸው። ለዚህ ያበቃቸውና ወያኔ ጥርስ ያስገባቸው በስልጣን ላይ ያለው መንግስት የሚያራምደው ፖሊሲ እንዲሁም የኢትዮጵያ አንድነት ጉዳይ ነው። ከመጀመሪያው ለእስር ያበቃቸው ምክንያት የሀገር አንድነትን ለማስጠበቅ ከአለቆቻቸው የወረደውን ትእዛዝ ተቀብለው ግዳጃቸውን በማከናወናቸው ነው። የታሰሩት መኮንኖች የሰሩት ጥፋት አለ ከተባለ እንደወታደር ከአለቆቻቸው የወረደውን ትእዛዝ በመፈፀማቸው ነበር። አልታዘዝም ማለት ይቻል ነበር ከሆነ ክርክሩ ሞኝነት ነው። ዛሬ የኢህአደግ መከላከያ ሠራዊት ግዳጅ ሲሰጠው አስቦበት ተወያይቶበት ይሆን ግዳጁን የሚወጣው? አይደለም ። ጉዳዩ በጥቅሉ ሲታይ ከቁንጫ ሌጦ ማውጣት ይመስላል። በቅርቡ የተኪያሄደው የኢትዮ - ኤርትራ ጦርነት መንግሥትን ምንም አላስተማረው ይሆን?

ኰሎኔል ብርሃነ መስቀል ከ17 ዓመት በላይ የእስር ቤት ቆይታቸውን ሲያስቡት ልባቸው ያዝናል። ሁለት ሴት ልጆቻቸው ተድረዋል። ሰርጋቸው ላይ አልታገኙም፤ እንደኣባትነታቸው ቆመው መዳር ነበር ምኞታቸው። ሙሽሮች ሲሸኙ የጉልበት መሳሙና የምረቃው ወግ ሳይደርሳቸው እንደቀልድ አለፈ። በቅርቡ ሴቷ ልጃቸው ለኣያትነት እንዳበቃቻቸው ሲሰሙ ደስ ተሰኙ። ሁሉም ደስታ ግን በስማ በለው እየሆነ አለፈ። እግዝአብሔርን ማማረር ስለማይወዱ ‘ለምን እኔ’ ብለው መጠየቁን ይጠላሉ። ሀገርን መውደድና ለሀገር መስዋእትነት መክፈል መጨረሻው ይሄ መሆኑ እጅግ ያሳዝናቸዋል፤ በቅርቡ ፍርድ ቤት ቀርበው ከተፈረደባቸው ወዲህ ከእስር የሚወጡበትን ቀን ለማወቅ ችለዋል። ጥቂት አመታት ናቸው የቀረቸው፤ ግን የነገ ጉዳይ ምንግዜም አያስተማምንም። ነገ የኛ አይደለምና፣ ግና ተስፋ የማይቆርጥ አሸናፊ ነው። ትእግስት ይጠይቃል እንጂ ሁሉም ያልፋል። እያለፈ የማይመልሱት ግን እድሜያቸው መሆኑን ሲገነዘቡ ቅሬታ ይሰማቸዋል። የትኛው ጋዜጣ ላይ እንዳነበቡት ትዝ አይላቸውም እንጂ ግጥሙን አእምረቸው ቀርፆ እስቀምጦታል። የእድሜን ጉዳይ ከራሳቸው ጋር ሲከራከሩ ግጥሙ ገላጋይነት ይገባል፤ -

ንጋት ኋላ ሸሽቷል፣
ከፊት ደግሞ መሽቷል።
እስቲ ምርኩዝ ላብጅ ልቤ ጠረጠረ፣
የእርጅና ነው ተራው ማደግማ ቀረ።

ከተከዙበት ቀና ብላው ሰማዩን አንጋጠው ሲመለከቱ ያ የሚወዱት በረራ ትዝ ይላቸዋል። እንደ እግር መንገድ እንዳልተመላለሱበት ሰማዩ እርሳቸውን ቁልቁል ብቻ ማየት ከጀመረ ከ17 አመት በላይ ተቆጠረ። ግዜ ወዳጅም ጠላትም ነው። ‘እስቲ ይሁን ’ ይላሉ በረጅሙ እየተነፈሱ። “ሁሉም ያልፋል ፣ ይህም ያልፋል”